

# NOVO NORDISK
# RESPONSE PROGRAM

## የፕሮግራም መረጃ

የ Novo Nordisk Response Program (www.nnrp.ca) ምንም አይነት የመድሃኒት ኢንሹራንስ ለሌላቸው እና የ Novo Nordisk ኢንሱሊኖች እና መርፌዎች ለመግዛት ገንዘብ ለሌላቸው በካናዳ ላሉ አዲስ የመጡ ስደተኞች እና ጥገኞች ነው።

## የፕሮግራም ዝርዝር መረጃ

የ Novo Nordisk Response Program የጥቅማ ጥቅም ካርድ ንቁ ከሆነበት ቀን ጀምሮ እስከ 120 ቀናት ባሉት ጊዜያት ውስጥ የተመረጡ የ Novo Nordisk ኢንሱሊን/ኖችን እና መርፌዎችን ያቀርባል።

ይህ ፕሮግራም ታካሚዎች የግል / ማሚያ የመድሃኒት ኢንሹራንስ እስከሚያገኙ ወይም ለህዝብ መድሃኒት ፕሮግራም እስኪያመለክቱ **ጊዜያዊ** ድጋፍ ለማቅረብ ታስቦ የተዘጋጀ ነው።

የ Novo Nordisk Response Program ንቁ በሆነ በ120 ቀናት ውስጥ የግል/ማሚያ ወይም የህዝብ መድሃኒት ኢንሹራንስ ከተገኘ፣ የ Novo Nordisk Response Program ጥቅማ ጥቅሞች ይህን ተከትለው ይቋረጣሉ።

## የፕሮግራም ጥቅማጥቅም ካርዶች

የ Novo Nordisk Response Program የጥቅማ ጥቅም ካርዶች ለታካሚዎች በጤና እንክብካቤ ባለሙያዎቻቸው ይሰጣሉ።

## ኢንሱሊን ሰጪ መሳሪያዎች ድጋፍ

- የ FlexTouch® መርፌ መውጋትን የሚያሳይ ገላጭ ቪዲዮ (እንግሊዘኛ)
- የ NovoPen® 4 መርፌ መውጋትን የሚያሳይ ገላጭ ቪዲዮ (እንግሊዘኛ)
- የ NovoPen® Echo® መርፌ መውጋትን የሚያሳይ ገላጭ ቪዲዮ (እንግሊዘኛ)

## ተጨማሪ ጥያቄዎች አሉዎት?

ስለ Novo Nordisk Response Program ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት፣ የ Novo Nordisk ደንበኛ እንክብካቤን በ1-800-465-4334 ያግኙ።

CA24DI00020 – 03/2024

# NOVO NORDISK
# RESPONSE PROGRAM

novo nordisk®

## የተካተቱ ምርቶች

| | |
|---|---|
| **Tresiba®** | 02467860 - Tresiba® Penfill®<br>02467879 - Tresiba® U-100 FlexTouch®<br>02467887 - Tresiba® U-200 FlexTouch® |
| **NovoRapid®** | 02467860 - Tresiba® Penfill®<br>02244353 - NovoRapid® Penfill®<br>02245397 - NovoRapid® Vial |
| **Levemir®** | 02271842 - Levemir® Penfill® |
| **NovoMix®** | 02265435 - NovoMix® 30 Penfill® |
| **Novolin® ge 30/70** | 02025248 - Novolin® ge 30/70 Penfill®<br>02024217 - Novolin® ge 30/70 Vial |
| **Novolin® ge NPH** | 02024268 - Novolin® ge NPH Penfill®<br>02024225 - Novolin® ge NPH Vial |
| **Novolin® ge Toronto** | 02024284 - Novolin® ge Toronto Penfill®<br>02024233 - Novolin® ge Toronto Vial |
| **መርፌዎች** | NovoFine® 32G Tip etw x 6 mm |

## NovoPen® ተገኝነት

የ **NovoPen® 4** መሳሪያዎች ለታካሚዎች ያለምንም ወጪ በፋርማሲው ውስጥ ይገኛሉ።

የ **NovoPen® Echo®** መሳሪያዎች በጤና እንክብካቤ ባለሙያው ቢሮ ወይም በአካባቢ የስኳር በሽታ ትምህርት ማዕከል ውስጥ በጥያቄ ሊገኙ ይችላሉ። በተጨማሪም፣ ፋርማሲስቶች በተወሰነ መጠን የ NovoPen® Echo® መሳሪያዎችን የ Novo Nordisk የደንበኞች እንክብካቤን በሚከተለው ስልክ ቁጥር በማነጋገር ሊጠይቁ ይችላሉ፡- 1-800-465-4334.

በዚህ ፕሮግራም ውስጥ የሚካተቱት ምርቶች የ Novo Nordisk Canada Inc.
በራስ የሚወስንባቸው ሲሆኑ ያለምንም የቅድሚያ ማስታወቂያ መለወጥ የሚችሉ ናቸው።

CA24DI00020 – 03/2024



# NOVO NORDISK
# RESPONSE PROGRAM

## በተደጋጋሚ የተጠየቁ ጥያቄዎች

**← የጥቅማጥቅም ካርዱ ከአንድ የ Novo Nordisk መድሃኒት በላይ  ጥቅም ላይ መዋል ይችላል?**

አዎ ይችላል! የ Novo Nordisk Response Program የጥቅማ ጥቅም ካርድን ለአንድ ሽፋን ላለው ህክምና ወይም ለማንኛውም ቅልቅል ሽፋን ላለው የ Novo Nordisk ኢንሱሊን ማግኘት ይቻላል።

**← የ Novo Nordisk Response Program ጥቅማጥቅም ካርድ ከአንድ ጊዜ በላይ ጥቅም ላይ መዋል ይችላል?**

አዎ ይችላል! ተመሳሳይ የ Novo Nordisk Response Program የጥቅማ ጥቅም ካርድ እስከ 120 ቀናት ድረስ ለኢንሱሊን መሞላት ሊያገለግል ይችላል። እንዲሁም፣ የ Novo Nordisk Response Program በአንድ የጥቅማ ጥቅም ማግኛ ካርድ 1 ሳጥን መርፌዎችን (ቢበዛ 4 ሳጥኖች የሚያክል)  ያቀርባል።

**← የ Novo Nordisk Response Program የጥቅማጥቅም ካርድ ጊዜው ሊያልፍበት ይችላል?**

የ Novo Nordisk Response Program ወደ ካናዳ ለሚመጡ አዲስ ሰዎች ጊዜያዊ እረፍት ለመስጠት ታስቦ የተዘጋጀ ነው። የፕሮግራሙ ጥቅማ ጥቅም ካርድ የተመረጡ የ Novo Nordisk ኢንሱሊን እና መርፌዎችን 120 ቀናት ድረስ እንዲያኙ ያረጋግጣል። በእነዚያ 120 ቀናት ውስጥ፣ ፕሮግራሙን የሚያገኙ ሰዎች የግል/ማሚያ የመድሃኒት ኢንሹራንስ እንዲገዙ ወይም ለተለያዩ የክፍለ ሃገር እና የብሔራዊ የህዝብ መድሃኒት ፕሮግራሞች እንዲያመለክቱ ይበረታታሉ።

የ Novo Nordisk Response Program ንቁ በሆነ በ120 ቀናት ውስጥ የግል/ማሚያ ወይም የህዝብ መድሃኒት ኢንሹራንስ ከተገኘ፣ የ Novo Nordisk Response Program ጥቅማ ጥቅሞች ይህን ተከትለው ይቋረጣሉ።

**← ለተካተተው የ Novo Nordisk ኢንሱሊን ማናቸውም አይነት ወጪዎች ወይም ክፍያዎች አሉ?**

የሉም። የ Novo Nordisk Response Program የሚሸፍነው በ Novo Nordisk የተደረገውን የመድሃኒት እና የመርፌ ወጪ እንዲሁም የኢንዱስትሪ ደረጃ ማከፋፈያ እና ማሰራጫ ክፍያዎችን ነው።

**← በ Novo Nordisk Response Program ውስጥ መርፌዎች ተካትተዋል?**

የተመረጡ መርፌዎች በዚህ ፕሮግራም ተካትተዋል። የ Novo Nordisk Response Program በአንድ የጥቅማ ጥቅም ካርድ ማግኛ ውስጥ 1 ሳጥን መርፌዎችን (ቢበዛ 4 ሳጥኖች የሚያክል) ያቀርባል።

**← ስለ የተለያዩ የክፍለ ሃገር እና የብሔራዊ  የህዝብ መድሃኒት ጥቅማ ጥቅም ፕሮግራሞች ተጨማሪ መረጃ ከየት ማግኘት እችላለሁ?**

ለተጨማሪ መረጃ በካናዳ መንግስት ድህረ ገጽ ላይ የተቀመጠውን የክፍለ ሃገር እና ብሔራዊ የህዝብ መድሃኒት ፕሮግራም ገፅን ይጎብኙ።